# በኢትዮጵያ ስግብርና ተብሎ «ስኢንቨስተሮች» «በሊዝ» እየተጡ ስሳሉ ስም መሬቶች አንዳንድ ነጥቦች

በአለማየሁ ኃ/ማርያም

ከጥቂት ጊዜ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሥርዓት «የአለቆች ሁሉ አለቃ» - capo di tutti capi - ኮንግሬስማን ዶናልድ ፔይን ለኤች. አር. 2003 ("Ethiopian Democracy and Accountability Act) ግፊት በማሳደራቸው ሸንቁጠዋቸው ነበር:: በሚታወቁበት ጫሌነት ምላሻቸውን ሰጥተዋል:- «ኢትዮጵያ፣ ይህ መንግስት እና ይህቺ አገር» እንደ «ባናና ሪፐብሊክ» አይነት ተደርጋ ከ«ካፒቶል ሂል» ወይም ከሌላ ስፍራ ልትመራ አይቻላትም፣ አትፈቅድም እንዲሁም ብቃቱ የላትም::» ያ ዛሬ በትክክል እወነት አይደለም:: ያለው መረጃ የሚያሳየው «ኢትዮጲያ እና ይህ መንግሥት» ከጅዳ ወይም ከተቀሩት ገልፍ አገሮች እንደ «ገብስ ሪፐብሊክ» ሊመሩ «ይቻላቸዋል፣ ይፈቅዳሉ እና አቅሙ» ያላቸው መሆኑን ነው:: የሳኡዲ እና ሌሎች የገልፍ «ኢንቨተሮች» ለራሳቸው የተትረፈረፈ የእርሻ ምርቶችን ለማቅረብ - የሚያስገርመው ከዓለም ገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶቹን ለማግኘት መቻላቸወ ነው - ከቀረጥ እና ከሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ነፃ ተደርገው ለም የእርሻ መሬት ለመግዛት (በ«ሊዝ») ከ200 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ወጭ ማድረጋቸው በስፋት ተዘግቧል::

ይህን የበርካታ ሚሊዬኖች የመሬት ሽያጭ («ሊዝ») የሚመለከቱ በርካታ የሚገርሙ ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ፣ «ኢንቨስተሮች» በሚል ሽፋን የሥርዓቱ «መሪዎች» ለውጭ መንግስታት የአገሪቱን ሰፋፊ መሬት እየሸጡና ኪሳቸውን እያደለቡ ባለበት ሰአት፣ ሩብ የሚጠጋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ችጋር ተጋርጦበታል:: የተቀረው ሕዝብ በየእለቱ ባልተመጣጠነ የምግብ እጥረትና በረሀብ እየተቆላ ነው:: ሁለተኛ፣«መሪዎቹ» የኢትዮጲያ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጡ በተቀረው ዓለም ሰላም የሚነሳ የማስጠንቀቂያ ደወል እንዲያቃጭል እያደረገ ባለበት ሰአት እነርሱ የ«ኢንቨስተር» አገሮቹን የምግብ ዋሰትና ለመጠበቅ እየተውተረተሩ ይገኛሉ:: ለባለፈው ዓመት የተ.መ.ድ የምግብና የእርሻ ድርጅት እየጨመረ ከላው የምግብ ዋጋ የኢትዮጵያ ድሃዎችን ለመጠበቅ አፋጣኝ እርምጃዎች ይወሰዱ ሲል ጥሪውን እያቀረበ ይገኛል:: ከሁለት ሳምንት አስቀድሞ የተ.መ.ድ ዓለም አቀፍ የምግብ ፕሮግራም ሙያዊ ምክሩን አወጥቷል:- ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው አገር አቀፋዊ እርዳታ ለሁለተኛው ሩብ ዓመት ያስፈልጋል ተብሎ ከተገመተው የ178 ሺህ ሜትሪክ ቶን ያህል እጥረት እንደሚያጋጥም ግምቱን ሰጥቷል:: ሶስተኛ፣ በቁስል ላይ እንጨት እንደመስደድ - ይኸው ሥርዓት «ኢንቨስተሮች»

ከተባሉት በተገኘው ራሱን ካበለፀገ በኋላ በዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ በዩ.ኤስ. መንግስት በአውሮፓ ሕብረት እና በሌሎች ለጋሽ አገራት ደጃፎች አይኑን በጨው አጥቦ የምግብ እርዳታ ይለማመጣል:: እንዲያ ነው እፍረት የለሽ «ተጠያቂነት የሌለው ሥርዓት» ጽናት!

ሁሉም በዓለም ዙሪያ ያሉ በዚህ በኢትዮጵያ እየተካሄደ በሚገኘው ሽያጭ ወይም አፍቃሬ-ንዋይ ስምምነተ ተደናግረዋል:: «ዘ ኢኮኖሚስት» መጽሔት - ውልፍት የማይል የወግ-አጥባቂዎች መቀመጫ እና የነፃ ገበያ እና ግሎባላይዜሽን አቅንቃኝ - ፍፁም በመደነቅና ግራ በመጋባት ጥያቄ ይጠይቃል:- «. . .እነኝህ የ«መሬት ይዞታዎች»፣ «የኒዎኮሎኒያሊስቶች» ዝርፊያ፣ ከ19ኛው ክ/ዘ ኮሎኒያሊዝም የሚለዩቱ ሌሎች ባለቤቶችንና ኤሊቶችን የሚያበለጽጉ በመሆቸው ምክንያት ብቻ ነው?» ሌላው ቀርቶ ግራ-ዘመሙ «ኢንዲፔንደንት» ጋዜጣ አግባብነት ያለውን ቁጭቱን ገልጿል:- «ባለፉት ጥቂት ወራቶች፣ የሳኡዲ አረበያ ኢንቨስተሮች ጦርነተ ባገሳቆላት አገር ውስጥ አስቀድመው ከያዟቸው መሬቶች በተጨማሪ በሚሊዮኖች ሄክታር ስንዴና ገብስ ለማብቀል ተስፋ በማድረግ 100 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በኢትየጵያ ውስጥ ለእርሻ መሬት ግዢ አውጥተዋል:: . . . ኒዎኮሎኒያሊስቶች የእርሻ መሬት በአፍሪካ ውስጥ እየሸመቱ ናቸው፣ የአገር ውስጥ ገበሬዎችን የሚጠብቃቸው ዓለም አቀፍ ሕግ ከሌለ በስተቀር እንክትክታቸው ይወጣል:: . . .» እንዲሁም እንደዚያ ያለውን ምስጢራዊና አድሎአዊ ስምምነቶችን በዓለም ያሉ ኤክስፐርቶች «የአፍሪካ አምባገነኖች እንደ ሱስ የተጠናወታቸውን ስር የሰደደ የሙስና ባህልን የሚያባብስ እንጂ ለአፍሪካ ልማት አንዳች ተጨባጭ አስተዋጽኦ አይኖረውም» በሚል መከራከሪያ በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ የማይቀበሉ ቡድኖችን ተቀላቅለዋል::

የውጭ የግል ካምፓኒዎች በማደግ ላይ ካሉ አገሮች የግል ባለንበረቶች መሬት በመግዛት የትላልቅ የእርሻ ማሳዎች ባለቤት የነበሩበት ጊዜ ነበር:: በማዕከላዊ አሜሪካ «ባናና ሪፐብሊኮች»፣ በበርካታ አገሮች የሚንቀሳቀሱ ኮርፖሬሽኖች ጥገኝነትንና የበታችነትን ያመጣ ኦሊጋሪኪ በመፍጠር በርካታ ጎስቋላ አራሾችን በዝብዘዋል:: የአሜሪካ ፍሪፍሬ አምራች ካምፓኒዎች በሂደት፣ ጠቅላላውን የነዚህን አገሮች የኤክስፖርት ሴክተር በበላይነት ለመቆጣጠርና እንደ ባቡር መስመሮች፣ማዕድን ማውጫዎችንና ወደቦችን የመሳሰሉ ቁልፍ መሰረተ-ልማቶችን በባለቤትነት ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸውን ጉልበት አግኝተዋል::

ዛሬ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች እየተመለከትን ያለነው ምንድን ነው የለየለት የ«ባናና ሪፐብሊክ» በሽታ ምልክት ነው:: በገብስ ሪፖብሊኳ ውስጥ ሊመሰረት የታቀደው ራሱን ችሎ የሚቆም ኢኮኖሚ መፍጠር ነው ወይም ሙሉ በመለና ፍፁም ከአገሪቷ ኢኮኖሚ የተነጠለና ግንኙነት የሌለው ኢኮኖሚ መፍጠርን አላማው ያደረገ ነው:: ብቸኛ

ግቡም የእርሻ ምርቶችን አምርቶ መልሶ ወደ «ኢንቨስተሮቹ» ኤክስፖርት ማድረግ ነው፡፡ በተያዙት መሬቶች ይቋቋማሉ ተብለው የሚጠበቁት የእርሻ ማሳዎች በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚካሄዱ ናቸው ተብለው የሚጠበቁ ናቸው - ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ብርጥ ዘሮችን፣ ፀረ-ተባዮችን እና ሌሎች የማምረቻ መንገዶችን የሚጠቀሙ፡፡ የሚቋቋሙት «በርካታ እርሻዎች» ከአስተናጋጇ አገር አጠቃላይ ኢኮኖሚ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የአገር ውስጥ ሰራተኞች እምብዛም ስልጠና ወደ ማይጠይቁ ስራዎች ዝቅ ይደረጋሉ፡፡ ለእነዚህ «ኢንቨስተሮች» የሚያከብሯቸው አካባቢያዊ መስፈርቶች ጥቂት ናቸው፣ በመሆኑም በአካባቢው የስነ ህይወት መስተጋበር ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር የሚያስችል መንገድ አይኖርም፡፡ በአጭሩ፣ በገብስ ሪፐብሊክ የሚፈጠረው ራሱን የቻለ ኢኮኖሚ፣ ኢኮኖሚው ለሚገኝበት አካባቢና በብሔራዊ ደረጃ ለአጠቃላዩ ኢኮኖሚ የሚሰጠው ጥቅም አነስተኛ ነው፡፡ በተጨማሪ ከ«ኢንቨስትመንቶቹ» አሰተናጋጇ አገር የምታገኘው ትርፍም በጣም አነስተኛ ነው የሚሆነው፡፡

በተ.መ.ድ የምግብና እርሻ ድርጅት፣ በ«ኢንተርናሽናል ፈንድ ፎር አግሪካልቸራል ዴቨሎፐመንት»፣ እና በ«ኢንተርናሽናል ኢኒስቲቱት ፎር ኢንቫይሮመንት ኤንድ ዴቬሎፐመንት» በተዘጋጀ ጥናት ጠቅላላው ስምምነት «ሥርዓት እንዳልተከተለ» ግልጽ መሆኑን ይጠቁማል፡-

«ለምሳሌ በኢትዮጵያ በኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን በክልል ደረጃ በተደረገ ጥናት የተገኘ መረጃ 22 ፕሮፖዛሎች ወይም የተፈፀሙ የመሬት ስምምነቶች ውስጥ 9ኙ ከ1 ሺህ ሄክታር በላይ ናቸው፡፡ ይህ በብሔራዊ ኢንቨስትመንተ ፕሮሞሽን ኤጀንሲ ከተመዘገቡት 148 ስምምነቶች በተጨማሪ ነው፡፡ በሌሎች ክልል መንግስታት ያሉ ኤጀንሲዎች ተጨማሪ የተመዘገቡ ፕሮጀክቶችና የተወሰኑ ያልተመዘገቡ ይዞታዎች ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በ2008 በኢትዮጵያ በእቅድ ደረጃ ያሉ ወይም ስምምነት የተደረሰባቸው መሬቶች ስፋትን በተመለከተ መረጃ አልተገኘም፡፡ በሌላ ምሳሌ «በኢትዮጵያ በጀርመኑ «ፍሎራ ኢኮፓወር» የተካሄደው ኢንቨስትመንት 13 ሺህ ሄክታር እንደሆነ ሪፖርት ቢደረግም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ የተመዘገበው ግን 3800 ሄክታር ብቻ ነው፡፡»

እላይ በተጠቀሰው ጥናት መሰረት፡-

«በኢትዮጰያ ወስጥ ለምሳሌ በብሔራዊ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ የተመዘገቡ ሁሉም የታደሉ መሬቶች ቀድሞ የሚጠቀምባቸው የሌላቸው «ጥቅም-የለሽ መሬቶች» ተብለው የተገለፁ ናቸው፡፡ ሆኖም 75 ሚሊዬን የሚጠጋ የሕዝብ ቁጥር ባላትና አብላጫው በገጠራማ አካባቢ በሚኖርባት አገር ይህ ይፋዊ ምደባ ጥያቄ የሚስነሳ ነው፡፡ በአገር ውስጥ ጥናት የተሰበሰበ መረጃ የሚጠቁመው ቢያንስ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ

ለኢንቨስተሮች የተሰጡ የተወሰኑ መሬቶች ማሳን እያፈራረቁ ለመጠቀምና ለበጋ ወቀት ግጦሽ ከዚህ ቀደም በጥቅም ላይ ይውሉ እንደነበር ነው።

ምንም እንኳን መንግስት እነዚህ በሊዝ ተሰጡ የሚላቸው የተወሰኑት መሬቶች የተሰጡት በክልል መንግስታት ነው ቢልም ያለው መረጃ የሚያረጋግጠው ተቃራኒውን ነው፡-

-አብዛኞቹ የመሬት ሊዞች የተሰጡት በፌዴራል መንግስት ነው። ይህ በኢትዮጰያ የተመዘገቡ 100% ጉዳዮችን ያጠቃልላል። መንግስት የመሬት ስምምነቶቹ ብልፅግናንና ስራን ለኢኮኖሚ ያመጣል የሚለው እንዲሁ ውሸት ነው። መረጃው የሚያሳየው «ኢንቨስተሮች» በጠራራ ፀሀይ አገሪቷን እየሞጨለፏት መሆናቸውን ነው፣

-በአገር ውስጥ የተሰራ ጥናት የመሬት ዋጋ በገንዘብ ሲተመን ዝቅተኛና ለድርድር አላስፈላጊ አካል እንደሆነ አጠቃላዩ ምልከታ እንደሚያረጋግጥ ያሳያል። በኢትዮጵያ በጥልቅ ከተመረመሩ ስድስት የስምምነት ፕሮጀክቶች ውስጥ አራቱ ዋጋቸው በየዓመቱ በአንድ ሄክታር ከ3-10 የአሜሪካ ዶላር የሚከፈልባቸው ሲሆን በአለም አቀፍ እይታ ክፍያው ዝቅተኛ ነወ፤ ምንም እንኳን የመሬት ኪራይ (ለምሳሌ በኢትዮጰያ ኦሮሚያ ክልል) ዋጋ ከፍ እያለ ቢሄድም። በርካታ ስምምነቶች - በዚህ ጥናት ከታየው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የተደረገውን ውል ጨምሮ - ለአምስት አመት ከግብር ነፃ የተደረጉ ናቸው። (አንቀጽ 4(ሀ) የቤኒሻንጉለ ጉመዝ ክልል ኮንትራት)። . . . ለምሳሌ በኢትዮጵያ (በአሜሪካ ዶለር በየዓመቱ በአንድ ሄክታር 20 የተገመተ) የትርፍ ግብር አብዛኛውን ጊዜ ለአምስት አመት ነፀ ነው፤ ከተሰጡና ዶክመንት ከተደረጉ 602 760 ሄክታር ፕሮጀክቶች እያንዳንዱ ፕሮጀክት በአምስት ዓመት ውስጥ ከግብር ነፃ የሚደረጉት 60 ሚሊዮን 276 ሺህ ከ42 ሳንቲም እንደሚደርስ ተገምቷል።

ይህ ስምምነት ነው ከጥቂት ወራት በፊት የሳኡዲ አረቢያ ንጉስ ኢትዮጵያ ከሚገኙ እርሻዎች ወደ አገራቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በገባላቸው ምርት ምክንያት በፌሽታ እንዲፈነጥዙ ያደረጋቸው።

በ19ኛው ክ/ዘ አወሮፓውያን አፍሪካን በሚቀራመዱበት ወቅት እና ከእንደገና ባለፈው ክ/ዘመን የጣሊያንን ወረራ ማምለጥ እና ለአላዊነቷንና ነፃነቷን በድል ማስጠበቋ እና በአዲሱ የኒዎኮሎኒያልስቶች አፍሪካን እርሻ የመቆራመድ ዘመቻቸው የመጀመሪያዋ ተጠቂ መሆኗ ታሪካዊ ቅኔ ነው የሚሆነው። . . .